# ትምህርተ ክርስቶስ

# ትምህርተ ክርስቶስ

- ትምህርተ ክርስቶስ፤
  - “ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ አካል ሆኖ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው፤ ለዘላለሙም እንደዚሁ ይኖራል።”

# የስልታዊ ነገረ መለኮት አስተምህሮዎች

የሥነ መለኮት (መግቢያ)

ትምህርተ መላእክት

ትምህርተ ቃለ እግዚአብሔር

ትምህርተ ሰው

ትምህርተ እግዚአብሔር

ትምህርተ ቤዛነት

ትምህርተ ክርስቶስ

ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን

ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ

ትምህርተ ነገረ ፍጻሜ

# የስልታዊ ነገረ መለኮት አስተምህሮዎች
# የስልታዊ ሥነ መለኮት ፍቺ

- ስልታዊ ሥነ መለኮት በማንኛውም ርእስ ላይ፤ ***“ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ ምን ያስተምረናል?”*** ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ማንኛውም ጥናት ነው።

ትምህርተ ክርስቶስ

ትምህርተ ክርስቶስ

የክርስቶስ ማንነት ዳሰሳ፤

የክርስቶስ ባሕርይ፤

ትምህርተ ግብረ ክርስቶስ፤

# ትምህርተ ክርስቶስ

## የክርስቶስ ማንነት ዳሰሳ፤

- ትምህርተ ክርስቶስ ማለት ምን ማለት ነው?
- ትምህርተ ክርስቶስ ለምን?
- *በአስተምህሮተ ክርስቶስ ላይ የተነሱ የስህተት ትምህርቶች እና ታሪካዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አቅዋም በትምህርተ ክርስቶስ ላይ፤*
- ክርስቶስ ማን ነው?
- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ምን ይላል?
  - ስለ ክርስቶስ የትንቢት ቃል እና ፍጻሜው፣
  - የአዲስ ኪዳን ምስክርነት፣
  - የክርስቶስ የምድራዊ ህይወቱ ዳሰሳ፣

# ትምህርተ ክርስቶስ

## የክርስቶስ ባሕርይ፤

- ክርስቶስን ማወቅ፥
- የክርስቶስ ባሕርይ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ፤
- ቅድመ ትሥጉት (ቅድመ ሥጋ መሆን)፤
- ድኅረ ትሥጉት (ድኅረ ሥጋ መሆን)፤
  - የክርስቶስ ፍጹም አምላክነት፤
  - የክርስቶስ ፍጹም ሰውነት፤

# ትምህርተ ክርስቶስ

## ትምህርተ ግብረ ክርስቶስ፤

- የትምህርተ ግብረ ክርስቶስ ዐውድ፤
  - የግብረ ክርስቶስ ልዩ ልዩ ጥቅልል ምሳሌዎች፣
- ክርስቶስ፥ ነብይ፣ ካህንና ንጉሥ መሆኑ፣
  - ክርስቶስ እንደ ነብይ፤
  - ክርስቶስ እንደ ካህን፤
  - ክርስቶስ እንደ ንጉሥ፤

# ትምህርተ ክርስቶስ

## ክፍል ፣

# ትምህርተ ክርስቶስ

## የክርስቶስ ማንነት ዳሰሳ፤

- ትምህርተ ክርስቶስ ማለት ምን ማለት ነው?
- ትምህርተ ክርስቶስ ለምን?
- *በአስተምህሮተ ክርስቶስ ላይ የተነሱ የስህተት ትምህርቶች እና ታሪካዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አቅዋም በትምህርተ ክርስቶስ ላይ፤*
- ክርስቶስ ማን ነው?
- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ምን ይላል?
  - ስለ ክርስቶስ የትንቢት ቃል እና ፍጻሜው፣
  - የአዲስ ኪዳን ምስክርነት፣
  - የክርስቶስ የምድራዊ ህይወቱ ዳሰሳ፣

# ትምህርተ ክርስቶስ

## የክርስቶስ ማንነት ዳሰሳ፤

- ትምህርተ ክርስቶስ ማለት ምን ማለት ነው?

# ትምህርተ ክርስቶስ

- ትምህርተ ክርስቶስ ማለት ምን ማለት ነው?
- *ትምህርተ ክርስቶስ፤*
  - *“ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ አካል ሆኖ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው፤ ለዘላለሙም እንደዚሁ ይኖራል።”*

    - *በአንድ አካል ሆኖ፤*
    - *ፍጹም አምላክ፤*
    - *ፍጹም ሰው፤*
    - *ለዘላለሙም እንደዚሁ ይኖራል፤*

# ትምህርተ ክርስቶስ

- ትምህርተ ክርስቶስ፤ . . .
  - ክርስቶስ፤ መሲሕ
    - ምን ማለት ነው?
      - ሥሩ “ክሪስቶስ” (“Χριστός”) የሚል የግሪክ ቃል ነው፤
      - “የተቀባ፣ ቅቡዕ” ማለት ነው።
      - በዕብራይስጥ መሲሕ ማለትና በግሪክ ክርስቶስ ማለት አንድ ናቸው፤
        - ቃሉ በአርባዕቱ ወንጌሎችና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ 82 ጊዜ ሲጠቀስ (ማቴዎስ [17]፣ ማርቆስ [7]፣ ሉቃስ [12]፣ ዮሐንስ [18] ሐሥ [28])
        - በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ከ200 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል።

# ትምህርተ ክርስቶስ

- ትምህርተ ክርስቶስ፤ . . .
  - ክርስቶስ የተቀባው በእግዚአብሔር ነው።

“የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ . . . ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና” **(ሉቃ 4፥17-19፤ ትንቢተ ኢሳይያስ 61፥1-3)**

- ክርስቶስ የተቀባው ለሦስት ሹመት ወይም አገልግሎት ነው፤
  - ለክህነት፣
  - ለንጉሥነት እና
  - ለነቢይነት።

- ስለ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ በሰፊው የተነገረው በወንጌላቱ ውስጥ ነው፤
  - ክርስቶስ ከየት እንደ መጣ፣
  - መጥቶ ምን እንዳደረገ፣
  - ከዚያም ወዴት እንደ ሄደ ተነግሯል፤
  - መቼ ተመልሶ እንደሚመጣ ባይነገርም ዳግመኛ እንደሚመጣ ግን ተስፋ ተሰጥቷል።

# ትምህርተ ክርስቶስ

## የክርስቶስ ማንነት ዳሰሳ፤

- ትምህርተ ክርስቶስ ለምን?

# ትምህርተ ክርስቶስ

- ትምህርተ ክርስቶስ ለምን? ለምን ትምህርተ ክርስቶስ አስፈለገ?
  - ትምህርተ ክርስቶስ፤ የክርስትና ዋና መሰረት ስለሆነ፥
    - በትምህርተ ክርስቶስ የምናየው የክርስቶስ ባህሪ፤ ስራና ክንውን ለክርስትና ቁልፍ መሰረት ነው፤ **(የማቴዎስ ወንጌል 16:15-18)**
  - ትምህርተ ክርስቶስ፤ ከሌለ ክርስትና ትርጉም የለውም (የሰማችንን መጠሪያ እንክዋን ያገኘነው ከክርስቶስ ነው፥ (ክርስቲያን - የክርስቶስ ተከታይ) **የቱ ክርስቶስ?**)
  - ትምህርተ ክርስቶስን እንደሚገባ ካላወቅን እና ካልተረዳን ለታላቅ ስህተት እንጋለጣለን፤ ክርስቶስ የወንጌል ማዕከል ስለሆነ፥ **(ወደ ገላትያ ሰዎች 1:8, ወደ ገላትያ ሰዎች 3:1, 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1:23-24)**

# ትምህርተ ክርስቶስ

## የክርስቶስ ማንነት ዳሰሳ፤

- በአስተምህሮተ ክርስቶስ ላይ የተነሱ የስህተት ትምህርቶች እና ታሪካዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አቅዋም በትምህርተ ክርስቶስ ላይ፤

# ትምህርተ ክርስቶስ

- በአስተምህሮተ ክርስቶስ ላይ የተነሱ የስህተት ትምህርቶች፤

| መጠሪያቸው | ኢባዮናይት Ebionites | ዶሲተስትስ Docetists | ኤሪያንስ Arians | አፖሊናሪያንስ Appollinarians | ነስቶሪያንስ Nestorians | ዩቲቾየንስ Eutychians |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወቅቱ | 2ኛው ክ/ዘ | 1ኛው ክ/ዘ መጨረሻ | 4ኛው ክ/ዘ | 4ኛው ክ/ዘ | 5ኛው ክ/ዘ | 5ኛው ክ/ዘ |
| የተካደው | የክርስቶስን አምላክነት | የክርስቶስን ሰውነት | የክርስቶስ አምላክነት | የክርስቶስን ሙሉ ሰውነት | የክርስቶስን አንድነት | የክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ሰውነት |
| ውግዘት | ታሪካዊ መረጃ የለም | ታሪካዊ መረጃ የለም | በኒቂያ ጉባኤ 325 ዓ/ም | በአንቲዮክ ጉባኤ 378-9 ዓ/ም በቀስጥንጥንያ ጉባኤ 381 ዓ/ም | በኤፌሶን ጉባኤ 431 ዓ/ም | በኬልቄዶን ጉባኤ 451 ዓ/ም |

# ትምህርተ ክርስቶስ

- ታሪካዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አቅዋም በትምህርተ ክርስቶስ ላይ፤

(1) የእግዚአብሔርን አንድነት ሳናፋልስ የክርስቶስን አምላክነት የምናጸናው እንዴት ነው?

(2) የክርስቶስን አምላክነት ሳንክድ ሰውነቱን የምናጸናው እንዴት ነው?

(3) የክርስቶስን አምላክነትና ሰውነት ሳናጣርስ ዋሕድነቱን የምናጸናው እንዴት ነው?

የኒቅያ ጉባኤ (325 ዓ.ም.) ለእግዚአብሔር አንድነትና ለክርስቶስ አምላክነት መልስ ሰጠ።

የኬልቄዶን ጉባኤ (451 ዓ.ም.) ለክርስቶስ አምላክነትና ሰውነት መልስ ሰጠ።

ነገረ ክርስቶስ ሁልጊዜ በውጥረት ላይ ነው፤ ከሰውነቱ ይልቅ አምላክነቱ የሚነላበት ወይም ከአምላክነቱ ይልቅ ሰውነቱ የሚነላበት ጊዜ አለ። እንግዲህ የሁለቱን ሚዛን መጠበቅ የቤተ ክርስቲያን የዘወትር የቤት ሥራ ሊሆን ነው።

# ትምህርተ ክርስቶስ

- ታሪካዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አቅዋም በትምህርተ ክርስቶስ ላይ፤ . . .

አራተኛው ታላቅ ጉባኤ፤ (የኬልቄዶን ጉባኤ በ451 ዓ.ም)
ክርስቶስ ሰውም አምላክም ከሆነ
“በአንድ አካል ሁለት ባሕርይ” - የምዕራቡ አብያተ ክርስቲያናት

“ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ” - የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የግብጽና የሶርያ አብያተ ክርስቲያናት ሁለተኛውን አገላለጽ ይቀበላሉ።”

የኦርዮንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት፤
በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት የመለኮትንና ትስብእትን <u>ተዋሕዶ</u> በማመን “አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ”

# ትምህርተ ክርስቶስ

- ታሪካዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አቅዋም በትምህርተ ክርስቶስ ላይ፤ . . .

አራተኛው ታላቅ ጉባኤ፤ (የኬልቄዶን ጉባኤ በ451 ዓ.ም)

“እንግዲህ ሁላችንም በአንድ ልብ ሆነን ቅዱሳን አባቶቻችንን ተከትለን በማይለወጥ በአንዱ ልጅና በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊታመኑ እንደሚገባ እናስተምራለን። እርሱ በመለኮት ፍጹም ነው፤ በሰውነትም ፍጹም ነው፤ በእውነት አምላክ ነው፤ በእውነትም ከነባቢት ንፍስና ከሥጋ የሆነ ሰው ነው። በመለኮቱ ከአብ ጋር ህላዌው አንድ ነው፤ በሰውነቱም ከእኛ ጋር በህላዌው አንድ ነው። ከኀጢአት በቀር እኛን የመሰለ፣ በመለኮቱ ቅድመ ዓለም ከአብ የተወለደ፣ በኋለኛው ዘመን ግን በሰውነቱ ስለ እኛ እኛን ለማዳን አምላክን ከወለደች ከድንግል ማርያም የተወለደ። መደባለቅ፣ መለወጥ፣ መለየት፣ መራራቅ ሳይኖር በሁለት ባሕርያት የሆነ፤ አንድ ልጅ ጌታ ክርስቶስ አንድና የማይለወጥ እንደ ሆነ ሊታመኑ ይገባል። ስለ መዋሐዳቸው የባሕርያት መለየት ሳይጠፋ አንድ አካልና አንድ ህላዌ በመሆናቸው በሁለቱ ባሕርያት የየራሳቸው ገንዘብ ተጠብቆ ይኖራል፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶ የእግዚአብሔር ቃል አንዱ የማይለወጥ ልጅ አንድ ልጅ ነው እንጂ፤ በሁለት አካላት የተለየና የተከፈለ አይደለም። ይኸውም አስቀድሞ ነቢያት እንዳስተማሩን ራሱ ክርስቶስ እንዳስተማረንና ከአባቶቻችን ሃይማኖት ውሳኔ እንደ ተቀበልነው ነው።”

# ትምህርተ ክርስቶስ

- ታሪካዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አቅዋም በትምህርተ ክርስቶስ ላይ፤ . . .

አራተኛው ታላቅ ጉባኤ፤ (የኬልቄዶን ጉባኤ በ451 ዓ.ም)
ክርስቶስ ሰውም አምላክም ነው።

## “አንድ አካል ሁለት ባሕርይ”

“ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ አካል ሆኖ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው፤ ለዘላለሙም እንደዚሁ ይኖራል።”

- በአንድ አካል ሆኖ፤
- ፍጹም አምላክ፤
- ፍጹም ሰው፤
- ለዘላለሙም እንደዚሁ ይኖራል፤